# በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማዕ/ጎ/ሀ/ስ ለደብረ ጎይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ካቴድራል ሰንበት ትምህርት ቤት የተሰጠ

# የክብረ ክህነትና የትምህርተ ኖሎት ኮርስ




አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ

**(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)**

ሰኔ ፲፰፣ ፳፻፲፰ ዓ.ም

# ክብረ ክህነት

ተክህነ-አገለገለ ከሚለው የግእዝ ግሥ ክህነት የሚል ዘር ይወጣል፡፡ ትርጉሙም አገልግሎት ማለት ነው፡፡ ክህነት ማለት በእግዚአብሔር ፊት ማገልገል፣ የአምልኮ ሥራ መሥራት፣ ስለራስና ስለሕዝብ ጸሎትና መሥዋዕት ማቅረብ፣ መባረክ፣ መቀደስ፣ ማጥመቅ፣ ማቊረብና የመሳሰለው መንፈሳዊ አገልግሎት ነው፡፡ ክህነት መንፈሳዊ ሹመት ነው፡፡ ካህን ማለት ደግሞ የእግዚአብሔር አገልጋይ፣ መንፈሳዊ አባት፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሆኖ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ ካህን እግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረውን ዓለም የሚመግብ፣ የሚያስተዳድርና የሚቆጣጠር ሹም ነው፡፡ የካህናት አለቃ (ሊቀ ካህናት) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሀብተ ክህነት በቅሚያ፣ በዝርፊያ ወይም በውርስና በግዥ ከአንዱ ወደ አንዱ የሚተላለፍ ሀብት ሳይሆን በመንፈሳዊ ጥሪ የሚተላለፍ ሀብት ነው፡፡ ክህነት መለኮታዊ የአገልግሎት ጥሪና ሰማያዊ ምርጫ ነው (ሉቃ.6፥13፤ ዮሐ.15፥16)፡፡ ክህነት ሰማያዊ ሹመት ነው (ሉቃ.10፥1)፡፡ ክህነት ለሰማያዊ አገልግሎት መለየት ነው (የሐዋ. ሥራ 13፥2-3)፡፡ ወደ ክህነት የሚመጣ ሰው መገንዘብ የሚገባው የሚያገለግለው እግዚአብሔርን፣ ቅድስት ቤተክርስቲያንን፣ ሕዝቡን እንጂ ራሱን ብቻ መሆን እንደሌለበት ነው፡፡ ክህነት ዕውቀትን ብቻ ሳይሆን ያወቁትን ያመኑትን ነገር በሕይወት ውስጥ እየገለጡ በእርሱም ጸንቶ መኖርን ይጠይቃል፡፡

## የክህነት ዋና ዓላማ

፩. በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ቆሞ ለማገልገል

፪. ትምህርታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሐዋርያዊነ ማኅበራዊ አገልግሎትን በሚገባ ለመፈጸም

፫. ለሀገርና ለወገን ዘወትር ለመጸለይ (የሐዋ. ሥራ 6፥4)

፬. ተግቶ ለማስተማር (የሐዋ. ሥራ 20፥20)

፭. የተጣሉትን ለማስታረቅ (ማቴ.5፥9)

፮. ሕሙማንን መጠበቅ፣ ማጽናናትና መፈወስ (ማቴ.10፥8፣ ያዕ.5፥14)

## ክህነት በሕገ ልቡና

ሕገ ልቡና የሚባለው ከአዳም እስከ ሙሴ ያለው ዘመን ነው፡፡ እግዚአብሔር ለአዳም ከሰጠው ሀብታት አንዱ ሀብተ ክህነት ነው፡፡ በዚህ ዘመን የነበሩ አባቶችም መሥዋዕትን በመሠዋት በክህነት አገልግለዋል፡፡ በመሥዋዕታቸውመ መልካም ምኞታቸው ተፈጽሞላቸዋል፡፡ ከመከራ ሥጋ ከመቅሠፍት ድነውበታል፡፡ ምሳሌ፡-

- አዳም (ኩፋ.5፥1)
- አቤል (ዘፍ.4፥4)
- ኖኅ (ዘፍ.8፥20-21)
- አብርሃም (ዘፍ.12፥7-9)
- ያዕቆብ (ዘፍ.31፥54)

## ክህነት በሕገ ኦሪት

- ካህናት የሚሆኑት በተለየ ከነገደ ሌዊ የተወለዱት ብቻ ነበሩ (ዘኍ.3፥6)
- በተለየ አምልኮ የሚፈጽሙባት፣ መሥዋዕት የሚሠዉባት ደብተራ ኦሪት ነበረች
- የራሱ የሆነ የክህነት አሿሿም ነበረ (ዘፀ.29፥6-8)
- ልዩ ልዩ የክህነት ክፍሎች ነበሩ (ዘፀ.28፥15)
- ነገሥታት ካህናትን የሚሽሩበትና የሚሾሙበት አጋጣሚ ነበር (1ኛ ነገ.2፥26-36)
- ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ቀን በምስክሩ ታቦት ላይ ወዳለው ወደ ሥርየቱ መክደኛ ወደ ተቀደሰው ስፍራ ይገባ ነበር (ዘሌ.16፥2)፡፡ ገብቶም ስለራሱና ስለሕዝቡ ይጸልይ ነበር (ዕብ.9፥7)፡፡
- ካህናቱ በመጀመሪያይቱ የድንኳን ክፍል በየጊዜው አገልግሎታቸውን ይፈጽሙ ነበር (ዕብ.9፥6)፡፡
- ልዩ ልዩ የመሥዋዕት ዓይነቶችን ያቀርቡ ነበር (ዘሌ.1፥9)፡፡
- በጠቅላላው ካህናት የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይፈጽሙ ነበር፡፡
    - የሕዝቡን ኃጢአት ማስተሥረይ (ዘሌ.4፥20)
    - የለምጽ ደዌን መለየትና ማንጻት (ዘሌ.13፥15)
    - መንፈሳዊ ፍርድ መስጠት (ዘዳ.17፥8-14)
    - የብሩን መለከት መንፋት (ዘኍ.10፥1-11)
    - ዕጣን ማሳረግና ሕሙማንን መፈወስ (ዘኍ.16፥4)
    - ታቦተ እግዚአብሔርን መሸከም (ኢያ.3፥1)
    - ነገሥታቱን ቀብቶ ማንገሥ (1ኛ ነገ.1፥32)
    - የእግዚአብሔርን ሕዝብ መገሠጽና ማስተማር (2ኛ ዜና መዋ.24፥20)
    - ሥርዓተ ቤተ መቅደስን ማክበርና ማስከበር (2ኛ ዜና መዋ.26፥16)
    - ስለሕዝብና ሀገር ድኅነት መጸለይ፣ መጾም፣ ማልቀስ (ኢዩ.2፥17)
- በእንተ ሌዋውያን፡- ከሌዋውያን የአሮን ልጆች ለተለየ ክህነት ሲመረጡ ሌሎች የሌዊ ልጆች ግን ለተቀረው የእግዚአብሔር አገልግሎት ተለይተዋል፡፡ የካህናቱ አገልግሎት የውስጥ የሌዋውያኑ አገልግሎት ደግሞ የውጭ ነበር፡፡ ከሌዋውያን ሥራዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡
    - የድንኳኑን ሥራ መሥራት
    - ንዋያተ ቅድሳትን መጠበቅ (ዘኍ.3፥7)
    - ካህናቱ ንዋያተ ቅድሳቱን ሸፍነው ከጨረሱ በኋላ ሰፈሩ ሲነሣ ንዋያተ ቅድሳቱን ሳይነኩ መሸከም (ዘኍ.3፥14)
    - በዜማ ዕቃዎች በመሰንቆና በበገና በጸናጽልም እያዜሙ የዝማሬ አገልግሎት መስጠት (1ኛ ዜና መዋ.6፥16-49)
- በእንተ ጸሐፍት፡- እነዚህም ከሌዋውያን ወገን ሲሆኑ ነገድ እንዳይፋለስ የትውልዱን ነገድ የሚጽፉ፣ ቃለ እግዚአብሔርንም የሚጽፉ ነበሩ (2ኛ ዜና መዋ.34፥13-14፣ ዕዝ.7፥11-13)
- በእንተ ካህናተ ጣዖት፡- ለጣዖት የሚሠዉ፣ ጣዖትን የሚያመልኩ ካህናት ካህናተ ጣዖት ይባላሉ (1ኛ ነገ.13፥33፤ 1ኛ ሳሙ.5፥5፤ ዳን.14፥7-11)

## ክህነት በሕገ ወንጌል

የሐዲስ ኪዳን ክህነት ጀማሪው ራሱ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዕብ.4፥14)፡፡ ከእርሱም ቀጥሎ ሐዋርያት ናቸው (ማቴ.28፥19)፡፡ ጌታችን ከሚከተሉት ሰዎች መካከል ለክህነት መርጦ ዓለምን እንዲያስተምሩ የላካቸው 12ቱን ሐዋርያት ነው፡፡ ሐዋርያትም ከደቀመዛሙርት መካከል የዲቁና ሹመትን የሰጧቸው መርጠው ለሰባቱ ዲያቆናት ነው፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግ በየደረጃው ያሉ ካህናትን ለመሾም በየጊዜው ልዩ ልዩ መሥፈርቶች ተሠርተዋል፡፡ የሐዋርያት ሥራም ማስተማር፣ ማጥመቅ፣ ማቍረብ ነበረ፡፡ የሐዲስ ኪዳን ካህናት ሥራ የሚከተለው ነው፡፡

- ማሰር መፍታት እና ቤተክርስቲያንን መጠበቅ (ማቴ.16፥18-20፤ የሐዋ.20፥28)
- ኃጢአትን ይቅር ማለት (ዮሐ.20፥22-24)
- ካህናትን መሾም (የሐዋ. ሥራ 6፥5-8፤ የሐዋ. ሥራ 13፥2-4)

ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት ምን ዓይነት መሆን እንደሚገባቸው በሚከተሉት ጥቅሶች ተገልጿል (1ኛ ጢሞ.3፥1፤ ቲቶ 1፥5-10፤ 1ኛ ጢሞ.5፥9-24)፡፡ ጌታ ካህናትን እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ ብሏቸዋል (ማቴ.28፥20)፡፡ የሐዲስ ኪዳን የክህነት ቅብብሎሽ ነቅዑ ወይም ምንጩ ክርስቶስ ነው፡፡ ቅብብሎሹም ያልተቋረጠ ነው፡፡ ካህን ሳይሆኑ የክህነት ሥራ የሠሩ ሰዎች ተቀሥፈዋል (ዘኊ.16፥1)፡፡ በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም ካህናት የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደመሆናቸው ክቡራን ናቸው፡፡ አገልግሎታቸውም ሰውን የሚያድንና የሚቀድስ በመሆኑ ክቡር ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም "በመስበክና በማስተማር የሚደክሙ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል" ብሏል (1ኛ ጢሞ.5፥17)፡፡ ክህነትን የሚሾም ሰው መልካም ምግባር ያለው መሆን ይገባዋል፡፡ ዐይነ ሥውር ክህነት መሾም አይገባውም፡፡ ይኸውም ነውር ሆኖ ሳይሆን ክህነቱ የሚፈልገውን አገልግሎት ማከናወን ስለማይችል ነው፡፡ አንድ ዓይና ጠንቅቆ ማንበብ የሚችል ከሆነና አንካሳ ደግሞ ዞሮ ማጠን የሚችል ከሆነ ምግባሩ ታይቶ ክህነት ሊሾም ይችላል፡፡

## መዓርጋተ ክህነት

የክህነት መዓርጋት ሰባት ናቸው፡፡ እነዚህም ዐፃዌ ኆኅት፣ መዘምር፣ አናጕንስጢስ፣ ንፍቀ ዲቁና፣ ዲቁና፣ ቅስና እና ጵጵስና ናቸው፡፡ ቆሞስነትን፣ ኤጲስ ቆጶስነትንና ሊቀ ጳጳሳትነትን ለየብቻቸው ከቆጠርናቸው ደግሞ ዐሥር ይሆናሉ፡፡ ዐፃዌ ኆኅት በወንዶች በር ሆኖ ያላመኑ ሰዎችና የተወገዙ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይገቡ የሚጠብቅ በር ጠባቂ ነው፡፡ አናጕንስጢስ በቤተክርስቲያን መጻሕፍትን ያነብ ዘንድ የሚሾም አንባቢ ነው፡፡ መዘምር በቤተክርስቲያን አገልግሎት ዳዊት የሚደግም ነው፡፡ ንፍቅ ዲያቆን መዓርጉ ከዲያቆን በታች የሆነ የዲያቆኑ ረዳት ነው፡፡ ንፍቅ ዲያቆን፣ አናጕንስጢስ፣ መዘምር፣ ዐፃዌ ኆኅት ያለአንብሮተ እድ እንዲሁ በቃል ብቻ በኤጲስ ቆጶሱ ይሾማሉ፡፡ ቄስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ፣ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ጳጳስ፣ ጳጳስ ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት፣ ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ቅዱስ ሲኖዶስ ሳለም ከሞተም በኋላ መፍታት ይችላል፡፡ ከሞተ በኋላ ቄስ ያወገዘውን ቄስ፣ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ፣ ጳጳስ ያወገዘውን ጳጳስ፣ ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት መፈታት ይችላል፡፡ በመዓርግ የበላዮች የበታቾቻቸው ያወገዙትን ሳሉም ከሞቱም በኋላ መፍታት ይችላሉ፡፡ ንፍቀ ዲያቆናትና ከዚያ በታች ያሉት ንዋየ ቅድሳትን መንካት አልተፈቀደላቸውም፡፡ በመቅደሱ በር አንጻር በቅድስት ቆመው ያገለግላሉ እንጂ፡፡ በር ዘጊዎች ለአንዲት ሰዓት እንኳ ከበሩ መለየት የለባቸውም፡፡ ዲያቆናዊትነትን የምትሾም

ሴት 60 ዓመት የሞላት መሆን አለባት። አገልግሎቷም በሴቶች መግቢያ በር ሆና ሴቶችን ታስተባብራለች።

## የጳጳሳት ግብር (ሥራ)

ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 5 ጳጳሳት የሚሾሙበትን፣ የሚሻሩበትንና ሊያደርጓቸው የሚገባቸውን ነገሮች በሰፊው ይናገራሉ። ጳጳሳት በዋናነት የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይገባቸዋል።

- ✓ ቅድስት ቤተክርስቲያንን በበላይነት መጠበቅና መምራት
- ✓ ችሎታና ብቃታቸውን እየመረመሩ ለዲያቆናት፣ ለቀሳውስትና ለመነኰሳት ሥልጣነ ክህነትን መስጠት
- ✓ ወንጌልን ያለ ፍርሀት መስበክና ሰባክያንን እያሰለጠኑ መላክ

በአንዲት ሀገር ሁለት ሰዎች ሊቀ ጳጳስነትን (ፓትርያርክነትን) አይሾሙም። ሊቀ ጳጳሳትን የሚሾመውም፣ ችግር ከተገኘበት የሚሽረውም ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ሊቀ ጳጳሳት ከታመመ እስከሚድን፣ የታሰረ እንደሆነ እስከሚፈታ ይጠበቃል። የማይድን ደዌ ከያዘውና ሊፈታ የማይችልበት እስራት ከሆነ በላዩ ላይ ሌላ ይሾማል። ኤጲስ ቆጶስ ብሉይ ሐዲስ የተማረ ሊሆን ይገባል። የሚመርጢት ሰዎች ሠላሳ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ናቸው። ሲሾምም በሊቀ ጳጳሳቱ (በፓትርያርኩ) ፈቃድና በምእመናን ምርጫ መሆን አለበት። ኤጲስ ቆጶስ በሹመቱ ጊዜ ሁለት ወይም ሦስት ኤጲስ ቆጳሳት ከጳጳሳት ጋር አንብሮተ እድ ያደርጋሉ። የሚሾመውም በዕለተ እሑድ ነው። በአንብሮተ እድ ኤጲስ ቆጶስን ሊሾሙ የተሰበሰቡ ኤጲስ ቆጳሳት እጃቸውን ይታጠባሉ። ከታጠቡ በኋላ በአንብሮተ እድ "ንሕነ ናነብር እደዊነ ዲበ ዝንቱ ገብር ኄሩይ ዘእግዚአብሔር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" እያሉ የቡራኬ ቃላትን እየተናገሩ ይሾሙታል። ከዚያ ለተሿሚው መስቀል ይሰጡታል። ዲያቆናት በሚሾመው ኤጲስ ቆጶስ ላይ አራቱን ወንጌል ዘርግተው ይይዛሉ። ይኸውም ወንጌልን ታስተምራለህ ሲሉ ነው። ኤጲስ ቆጳሳት ሲሾሙ ቅዳሴ ባስልዮስን መቀደስ ይገባል። ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ሦስት ሱባኤ ይጾማል። የተሾመበት ጊዜ በዓለ ኀምሳ ከሆነ በዚያ ጊዜ መጾም ስለማይችል አሳልፎ በዚያው ዓመት በየሱባዔው ሦስት ሦስት ቀን ጾሞ ይጨርሳል። ኤጲስ ቆጶስ በሃይማኖት ወደማይመስሉን ወደ አሕዛብ በዓል እንዳይሄድና እንዳያከብር ተከልክሏል። የኤጲስ ቆጶስ ቤቱ ከቤተክርስቲያን አጠገብ ሊሆን ይገባል። የኤጲስ ቆጶስ ስሙ በጸሎት በቅዳሴ ጊዜ ይነሣል። የክርስቶስን ሥጋና ደም ከኤጲስ ቆጳሳት ይቀበላል እንጂ ከቀሳውስት አይቀበልም።

## የቀሳውስት ግብር (ሥራ)

ስለቀሳውስት አሿሿም፣ ተግባርና ስለሚሻሩበት ሁኔታ በሰፊው የሚናገረው የፍትሐ ነገሥት ክፍል አንቀጽ 6 ነው። ቀሳውስት በዋናነት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይገባቸዋል።

- ያለፍርሀት ዞሮ ማስተማር፣ ማጥመቅ፣ ቀድሶ ማቊረብ፣ መናዘዝና ማጽናናት
- ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ጠብቆ ማስጠበቅ
- የተጣላን ማስታረቅ
- ለሙታን ጸሎተ ፍትሐትን ማድረግ

ሠላሳ ዓመት ያልሞላው ቅስና መሾም እንደሌለበት ፍትሐ ነገሥት ይገልጻል፡፡ ብሉያትን ሐዲሳትን ይህም ባይሆን አራቱን ወንጌል ያላወቀ ቅስና አይሾምም፡፡ ቀሳውስት ከኤጲስ ቆጶሱ ዘንድ በየዓመቱ ሦስት ጊዜ እንዲሰበሰቡ ታዝዘዋል፡፡ ቀሳውስትና ዲያቆናት በሥጋዊ ነገር ዋስ፣ ተያዥ፣ ምስክር መሆን አይገባቸውም፡፡

### የዲያቆናት ግብር (ሥራ)

ስለዲያቆናት በስፋት የሚናገረው የፍትሐ ነገሥት ክፍል አንቀጽ 7 ነው፡፡ ዲያቆናት በዋናነት የሚከተሉትን ተግባራት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

- ለተልእኮ ምሥጢር መፋጠን
- ለሚቀጥለው መዓርግ በሚያበቃቸው ትምህርት መትጋትና ማስተማር
- ቀሳውስትን በቃለ እግዚአብሔርና በመላላክ መርዳት
- በሽተኞችን፣ የተቸገሩትን መጎብኘት

ዲያቆን ምእመናን በቤተክርስቲያን እንዳይተኙ፣ እንዳይስቁ ይቆጣጠራል፡፡

## ትምህርተ ኖሎት

ኖለወ-ጠበቀ ከሚለው የግእዝ ግሥ ኖሎት የሚል ስም ይወጣል፡፡ ትርጉሙም ጠባቂዎች፣ እረኞች፣ መጋቢዎች፣ አስተዳዳሪዎች ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ትምህርተ ኖሎት የሚለው ቃል የእረኝነትን፣ የጠባቂነትን፣ የአስተዳዳሪነትንና የመጋቢነትን አደራ፣ ኀላፊነትና የዘወትር ተግባርን ያመለክታል፡፡ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ ማስገኘት ብቻ ሳይሆን የተፈጠረውን ዓለም መመገብ፣ ማስተዳደርና መጠበቅ የሚችሉ ወገኖችን መሾሙን ስንመለከት ቸርነቱን ዕፁብ ዕፁብ ብለን እናደንቃለን፡፡

### የኖላዊነት ተግባር

የኖላዊነት ተግባርን በሦስት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ እነዚህም፡-

- አምላካዊ ጥበቃ
- መልአካዊ ጥበቃ
- ሰብኣዊ ጥበቃ

ናቸው፡፡ አምላካዊ ጥበቃ ስንል እግዚአብሔር በባሕርዩ ፈጥሮ የሚጠብቀን መሆኑን ያመለክታል (መዝ.22፥5፤ መዝ.79፥1)፡፡ መልአካዊ ጥበቃ የምንለው እግዚአብሔር በቸርነቱ ፍጥረታትን ይጠብቁ ዘንድ መላእክትን ከማዘዙ የተነሣ የሚፈጸም ጥበቃ ነው (መዝ.33፥7፤ መዝ.90፥10-13)፡፡ ሰብኣዊ ጥበቃ የሚባለው ደግሞ እግዚአብሔር ፍጥረቱን በካህን፣ በንጉሥ አድሮ የሚጠብቅበት ጥበቃ ነው (ኤር.23፥1-5፤ ሕዝ.34፥1-10)፡፡ መልአካዊ ጥበቃና ሰብኣዊ ጥበቃ እግዚአብሔር ለጠባቂዎች ዋጋቸው ይበዛ ዘንድ የሰጣቸው ጥበቃ ነው እንጂ እርሱ መጠበቅ አልችል ብሎ እንዲያግዙት የመደባቸው ጠባቂዎች አይደሉም፡፡ በብሉይ ኪዳን ኖሎት የሚባሉ ነገሥታትና ነቢያት ነበሩ፡፡ አባግዕ (በጎች) የሚባሉ ደግሞ ሕዝቦች ናቸው (1ኛ ዜና መዋ.21፥17፤ ሕዝ.3፥7)፡፡ የሐዲስ ኪዳን ኖላዊነት የሚጀምረው ከባለቤቱ ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ፡፡ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል" እንዲል (ዮሐ.10፥11)፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ኖላዊነት የባሕርይ ነው፡፡ የፍጡራን ኖላዊነት ግን የጸጋ ነው፡፡ ሐዋርያት

በተሰጣቸው ጸጋ ይጠብቁ ዘንድ የኖላዊነት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። "በጎቼን፣ ግልገሎቼን፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ" እንዲል (ዮሐ.21፥16)። የካህናት ጠባቂነትና መጋቢነት የክርስቶስ የማዳን ሥራ በቤተክርስቲያን እንዲቀጥልና እንዳይቋረጥ የሚያደርግ ነው። ከመልካም ኖላዊ የሚጠበቀው በጎቹን መጠበቅና ማሰማራት ብቻ ሳይሆን የበጎቹን ሕይወት የሚያጠፋ ሲመጣ ላለማስነካት ለበጎቹ ተላልፎ መሞት ነው።

## የመልካም ኖላዊነት መገለጫዎች

- ኀላፊነትን መወጣት
- ወንጌልን ማስተማር
- ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን ማከናወን
- ችግረኞችን መርዳት
- ሥርዐተ አምልኮን መጠበቅና ማስጠበቅ
- አደራን መጠበቅና የመሳሰሉት ናቸው

## የንስሓ አባትና ልጅ ግንኙነት

ከሰባቱ የአባት ዓይነቶች አንዱ አበ ነፍስ (የነፍስ አባት) ወይም የንስሓ አባት ነው። ሰባቱ አባቶች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

- ልዑል እግዚአብሔር (ዘዳ.32፥6)
- ወላጅ አባት (ዘፀ.20፥12)
- አሳዳጊ አባት (ሉቃ.2፥48)
- የንስሓ አባት (ማቴ.8፥4)
- የክርስትና አባት (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 3)
- (ለመነኮሳት) የቆብ አባት (መጽሐፈ መነኮሳት)
- የቀለም አባት (1ኛ ጢሞ.1፥2)

ናቸው። የንስሓ አባት ለልጆቹ አርአያ መሆን ይገባዋል። በአጭሩ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ከንስሓ አባት ይጠበቃል።

- ለንስሓ ልጆቹ ሕይወት መጨነቅና መጠበብ አለበት
- የነፍስ ልጆቹን በአንድነትም ሆነ በተናጥል በወንጌል ትምህርትና በምክር ማነጽ አለበት
- በነፍስ ልጆቹ ዘንድ ያለውን ልዩ አባታዊ ክብር ከሚያሳጡ ተራ ጥቅማጥቅሞች ራሱን መጠበቅ አለበት
- የነፍስ ልጆቹን የአኗኗር ሁኔታ መለየት ማለትም የዕድሜ፣ የሥራ፣ የአመለካከት፣ የጋብቻ፣ የጠባይ ሁኔታዎችን መረዳት ይገባዋል
- ካህኑ በሀብታምና በድኻ፣ በአሠሪና በሠራተኛ፣ በተማረና ባልተማረ መካከል ልዩነት ማድረግ የለበትም
- ሁሉንም በእኩልነት ማገልገል ይገባዋል
- ካህን ሌላውን የሚጠብቅ ስለሆነ በቅድሚያ የራሱን ማንነት መቆጣጠር ይገባዋል ራሱንም መምራት ይገባዋል።

- በኑሮው ሁሉ ልክና መጠን ያለው ሊሆን ይገባል
- ካህን ተልእኮው እንዲሠምር መማር ግዴታው ነው
- ካህን ልቡ ቅን ገርም መሆን ይገባዋል። ሰው እንደመሆኑ መጠን ከወንድሙ ጋር የሚያጣላ ነገር ቢገጥመውም ሳይውል ሳያድር መታረቅ፣ ሰላምን መፍጠር ያስፈልገዋል። ሐዋርያት ቃለ ሕይወትን ሲያስተምሩ ለሚደርስባቸው መከራና ግፍ በብድራት ለመመለስ ቂም በቀል የሚባል ከቶ አያውቁም ነበር።
- ካህን የማይሰክር መሆን አለበት። ስካር ትልቁን ትንሽ የሚያደርግ፣ የተከበረውን የሚያዋርድ ነውና።
- ከፍቅረ ንዋይ መራቅ አለበት
- ካህን ለአንደበቱ ውሸትን ማስለመድ የለበትም። የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደመሆኑ ለምእመናን እውነትን ያስተምር እንጂ።

የወንጌል ትምህርት ጎልቶ የሚታየው በአስተማሪው ሕይወት ሲተረጎም ነው። የእግዚአብሔር መልእክተኞች ካህናት ማሕበራዊ ችግርና ግጭት ባለበት ቦታ ተገኝተው ለችግሩ መፍትሔ የሚያስገኙ መሆን ይገባቸዋል። የጸብ፣ የክርክር፣ የግጭት መጨረሻው መተላለቅ ነውና። ካህናት የንስሓ ልጆቻቸው በየጊዜው ይቆርቡ ዘንድ ማስተማር አለባቸው። ምክንያቱም ቁርባን ምእመናንን ከእግዚአብሔር፣ ምእመናንን ከምእመናን አንድ ያደርጋልና። ምእመናን የዘር፣ የዕድሜ፣ የፆታ ልዩነት ሳያደርጉ ከአንድ ጻሕል በልተው ከአንድ ጽዋዕ ጠጥተው የአንድ ሕይወት ተካፋዮች የአንድ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለንና።